# በግንቦት 7 እና አዴሃን መካከል የተፈጠረውን ውዝግብ አሁንም እንደቀጠለ ነው!

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በውህደት ስም የኢትዮጵያ ህዝቦች አርበኞች ግንባር (ኢ.ህ.አ.ግ.) ህልውናን በማክሰም በርካታ አመራሮቹ በሻዕቢያ እንዲታሰሩ ካደረገ በኋላ በአማራ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ ሃይል (አ.ዴ.ሃ.ን.) ላይ ተመሳሳይ ደባ ለመፈፀም እንቅስቃሴ በመጀመሩ ምክንያት በሁለቱም ድርጅቶች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ወደፍጥጫ ማምራቱን እና በዶ/ሩ መሰሪ ድርጊት የተበሳጩ ከ80 በላይ የቀድሞ ኢ.ህ.አ.ግ. አባላት ግንቦት 7ን ጥለው ከአ.ዴ.ሃ.ን. ጋር መቀላቀላቸው ኤርትራ ውስጥ የሚገኙ ምንጮቻችን ያደረሱን መረጃ በወቅቱ ማስተላለፋችን ይታወሳል።

በሁለቱ ድርጅቶች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት *“ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አዋርዶናል፣ እስካሁን ሲጫወትብን ቢቆይም የአማራ አደረጃጀት ካለው አዴሃን ጋር ሆነን ለአማራ ህዝብ እንታገላለን”* በሚል ቁጣ አሁንም ቁጥሩ የማይናቅ የኢ.ህ.አ.ግ. አባል ግንቦት 7ን ጥሎ ከአዴሃን ጋር እየተቀላቀለ እንደሚገኝ ምንጮቻችን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ስልጠና ወስደው በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ የአዴሃን ታጣቂ አባላት *“ያለምንም ስራ ኤርትራ ውስጥ መቀመጥ የለብንም፣ ወደ ሀገራችን ገብተን መስራት አለብን፣ የምንመገበው ምግብም እየተስማማን አይደለም”* የሚል የተቃውሞ ሃሳብ በማሰማታቸው ጥጋቡና ማሬ የተባሉ ሁለት የጋንታ አመራሮች *“ተቃውሞ አነሳስታችዋል”* ተብለው እንደታሰሩ ምንጮቻችን አክለው ገልፀዋል። ይህን ተከትሎ ህዳር 04 ቀን 2010 ዓ.ም በጥበቃ ሥራ ላይ የነበሩ ወርቁ ጌጡ፣ አፋራ ገዛኸኝ እና ንጉሴ ጃጃው የተባሉ የድርጅቱ አባላት ጠፍተው ወደ ኢትዮጵያ ሊሻገሩ ሲሉ ድንበር አካባቢ ከነበሩ የሻዕቢያ ወታደሮች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ አንድ የሻዕቢያ ወታደር ገድለው ለወያኔ እጃቸው እንደሰጡ ምንጮቻችን ገልፀውልናል።